Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY
PUBLIC SCHOOLS

# ለ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ዓመት የሚወስዱ የዳበረ የማንበብ እና መጻፍ ካሪኩለም (ELC) ትምህርት የወላጅ መመሪያ

በ5ኛ ክፍል እያሉ፣ ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጹት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ላይ ትምህርት ያገኛሉ።

## ELC ንባብ

| **1ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** | **2ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** |
|---|---|
| ተማሪዎች በርካታ የተመረጡ የ Junior Great Books Series 5 ስነጽሑፍ፣ ልቦለድ ያልሆኑ የጥያቄ ጽሑፎች፣ እና ከአሜሪካ አብዮት ማህበራዊ ጥናቶች ርዕስ ጋር የተዛመዱ ጽሑፎች በማንበብ፣ እርስ በእርሱ የመስማማት ዘዉግ፣ ርህራሄ፣ እና በማቻቻል አማካይነት ግንኙነቶችን ይመረምራሉ። የቅርበት ንባብ፣የተጋራ ጥያቄን መጠቀም፣ እና በሁለገብ (interdisciplinary) ትምህርት ዉስጥ መሳተፍ ተማሪዎች እንዲመረምሩ፣ እንዲያብላሉ/እንዲያዋሂዱ፣ እና በጥልቀት እንዲረዱ ይረዳቸዋል።<br><br>አደረጃጀት እና የጽሑፍ መዋቅሮችን፣ የጽሑፍ ባህሪያትን፣ኅራ-ተኮር ቃላትን ለመለየት፣ እና ለጠንካራ መረጃዊ ስራ ዝግጅት ለመጠቀም እንዴት በብቃት እና በዉጤታማነት ማስታወሻዎችን ለመውሰድ እንዲችሉ ተማሪዎች በማህበራዊ ጥናቶች እና በሳይንስ ውስጥ ያሉ የጥናት ርዕሶችን የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዊ ጽሑፎችን ያነባሉ። የተማሪዎችን ወሳኝ እና የፈጠራ አስተሳሰብ ችሎታቸውን ለማዳበር እና ለማጥራት የውይይት ሞዴሎች፣ የተለዩ የማስተማር ስልቶች፣ እና መልቲሚዲያ ፅሁፎች ጥቅም ላይ ይዉላሉ። | ብዙዎቹ የ Junior Great መጽሐፍት ምርጫዎች እና የ Jacob's Ladder ምርጫዎች በሳይንስ ውስጥ ካለው የጥናት ርዕስ ጋር ይዛመዳሉ። በእነዚህ የትምህርት ሪሶርሶች አማካኝነት፣ ተማሪዎች የቅርብ ንባባቸውን እና የትንተና ችሎታቸውን ማዳበር እና በጽሑፍ ምላሽ መስጠታቸውን ይቀጥላሉ። ከ Junior Great መጽሐፍት አንዱ የቅጥያ ትምህርት ተማሪዎች ስለ ምህንድስና ዲዛይን የተማሩትን በመጠቀም የመንሳፈፊያ ሰሌዳ ለመንደፍ የፈጠራ ችሎታዎችን ያነሳሳል።<br><br>ተማሪዎች እጅግ በጣም የሕልም አይነትን በሚያነቃቃ ሁኔታ በንባብ እና በፅሁፍ ተሞክሮዎች ይሳተፋሉ። የቅዠት ስዕል መጽሐፍቶችን እና ልብ ወለዶችን በማንበብ እና በማጥናት፣ ደራሲዎች ስለ ምናባዊ ዓለም፣ምታታዊ ገጸባህሪዎች፣ እና ሊታመኑ የሚችሉ ክስተቶች ገላጭ መቼቶች/ቅንብሮችን እንዴት እንደሚፈጥሩ ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ተማሪዎች በስነ-ጽሑፍ ክበብ ውስጥ ይሳተፋሉ። |
| **3ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** | **4ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** |
| ተማሪዎች የትኩረት ጥያቄ የሆነዉን "ሥነ-ጽሑፍ፣ ታሪክ፣ እና ዓለማችንን በተሻለ እንድንረዳ እንዴት ቅጦች/ፓተርንስ ሊረዳን ይችላል?" የሚለውን የዊሊያም እና ሜሪ የለውጥ ቅጥ/ፓተርን ዩኒትአካል የሆነዉን የሚመረምሩበት የትምህርት ተሞክሮዎች ዉስጥ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች የሁሉንም ፅሁፎች ሳይክሊክ የለውጥ ስርዓቶች/ቅጦችን/ፓተርንስ ሀሳብ ለማገናኘት ብዙ ግጥሞችን፣ አጭር ታሪክ፣ እና ልብ ወለድ ያነባሉ። ተማሪዎች በልበ-ወለዶች ውስጥ ለቤት-መራቅ-ቤት/Home-Away-Home የሴራ አወቃቀር ልዩ ትኩረት በመስጠት እናም በክፍል እና በትናንሽ የቡድን ውይይቶች ወቅት ለማጣቀሻነት የአስተሳሰባቸውን መጽሀፍ ያስቀምጣሉ/ይይዛሉ።<br><br>ተማሪዎች ለአሳማኝ ጽሑፋዊ መጣጥፎች ርዕስ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል፣ ስለ ሐቀኝነት እሴት ስለሚማሩ ገጸባህሪያት፣ የሁለቱ የ Junior Great Books ምርጫዎች ሁለተኛ የሆነዉን አንብበዉ ይጨርሳሉ። ከዚያ ተማሪዎች ወደ መረጃ ፅሁፎች ይሸጋገራሉ እና ከማህበራዊ ጥናቶች በይዘት ላይ ጠንከር ባለ መልኩ ይማራሉ። ተማሪዎች ከዌስትዋርድ መስፋፋት ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ልቦለድ ያልሆኑ የ Junior Great መጽሐፍት ምርጫዎች ያነቡ እና የራሳቸዉን የታሪክ መነጽር /The Lens of History፦ የምርምር ዘገባዎች አፃፃፍ ዩኒት ይጀምራሉ። | ተማሪዎች የዊሊያም እና ሜሪ የለውጥ ስርዓት/ቅጥ/ፓተርን ዩኒትላይ መስራታቸዉን በመቀጠል "ለውጥ በእምነታችን እና በድርጊታችን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው? ለሚለዉ የትኩረት ጥያቄ ምላሽ ይሰጣሉ። ተማሪዎች በመጽሐፎቹ ውስጥ ተመሳሳይነት እና ልዩነቶችን በማነፃፀር እና የሳይክሊክን የለውጥ ስርዓቶች ትንታኔ በመቀጠል እንዲሁም የጠቅላላውን የሳይክሊክ ማትሪክስ ዩኒት ለማጠናቀቅ እንደ መልህቅ ልብ ወለድነት በመጀመሪያዉ ልብ ወለድ ደራሲ የተጻፈ ሌላ ልብ ወለድ ያነባሉ ተማሪዎች ለተመረጡት የልበወለድ ምዕራፎች የቃላት እና የፅሁፍ ዌብ ከማጠናቀቅ በተጨማሪ፣ በማስታወሻዎቻቸው ላይ ማስታወሻዎችን መመዝገብ እና ጥያቄዎችን መመለስ ይቀጥላሉ።<br><br>ተማሪዎች ከተመረጡት የሳይንስ ልብ ወለድ ጽሑፎች ውስጥ ዩኒቱን/ክፍሉን በስነ-ጽሑፍ ክበብ ከመጨረሳቸዉ በፊት፣ ከ Jacob's Ladder የመረጃ ጽሑፍ በተጨማሪ ሁለቱንም ሥነ-ጽሑፋዊ እና መረጃ ሰጪ የ Junior Great መጽሐፍት ምርጫዎችን ያነባሉ። ይህ ዘውግ ለወደፊቱ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የሳይንሳዊ እና የቴክኖሎጂ እድገቶችን በተመለከተ ተማሪዎች ጥያቄዎችን ማንሳት እንዲችሉ አስተሳሰባቸዉን/አመለካከታቸዉን ያሰፋዋል። |

© 2019 ፈጣንና የዳበረ ትምህርት

**ELC ንባብ**

| 1ኛ የማርክ መስጫ ወቅት | 2ኛ የማርክ መስጫ ወቅት |
|---|---|
| ተማሪዎች በጽሑፍ ውስጥ በሉሲ ካልኪንስ የጥናት ዩኒት ውስጥ ትረካ እና የመረጃ ስራ ይጽፋሉ፦የትረካ ጥበብእና በግል ፍላጎት ላይ መጣጥፎችን መጻፍ። ተማሪዎች የትረካ አቀራረቦችን ይበልጥ ለማዳበር እንዲችሉ እና የትረካ ጽሑፍን ንጥረ ነገሮች በጽሑፍ ባህሪ ላይ ለመተግበር በአራተኛ ክፍል በተማሩት ችሎታዎች ላይ ይገነባሉ።<br><br>ተማሪዎች በዩኒቱ ዉስጥ በሙሉ በተራዘመ የጽሑፍ ፕሮጀክቶች እና ለንባብ በጽሑፍ በሚሰጡ የአስተያየት ምላሾች ውስጥ ይሳተፋሉ። | ተማሪዎች ምርምርን መሰረት ያደረገ የዉይይት መጣጥፎችሶስት የመከራከሪያ መጣጥፎችን ለመፍጠር መረጃ ሰጭ እና የአስተያየት ጽሑፍን የሚያጣምሩበትን ይጀምራሉ። ተማሪዎች ስለ ደራሲ አመለካከት ለመማር እና በጽሁፎች ዙሪያ መረጃን እንዴት ማዋሃድ እንደሚችሉ ለማወቅ በምርምር ቡድኖች ውስጥ ይሰራሉ። መረጃው ጠንካራ የክርክር ፅሁፎችን በመገንባት ክርክር ለማንሳት የሚያገለግል ነው። ተማሪዎች የመከራከሪያ ነጥቦችን/ሀሳቦችን (ማለትም የይገባኛል ጥያቄ፣ ምክንያቶች፣ ማስረጃ) የአጻፋ የይገባኛል ጥያቄ በማንሳት እና ክርክርሩን ዉድቅ ማድረጊያ በማቅረብ፣ እና አድማጩን በመሳቢያ/ማሳመኛ ዜዴዎች እንዴት እንደሚያጠናክሩ ይማራሉ።<br><br>የዩኒቱ የመጨረሻ ሳምንቶች ተማሪዎችን እጅግ በጣም የሕልም አይነት በሚያነቃቃ ሁኔታ በንባብ እና በፅሁፍ ተሞክሮዎች ያሳትፋሉ። ተማሪዎች የቅዠት/ሕልም ስዕል መጽሐፍቶችን እና ልብ ወለዶችን ያጠናሉ፣ የመጀመሪያውን የቅዠት/ሕልም ታሪክ ለመጻፍ በደራሲ የታተመ የቅዠት ጽሑፍ ያነሳሉ። |
| **3ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** | **4ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** |
| ተማሪዎች በ “If...Then...Poetry” አፈታሪክ ጽሑፍ ዩኒት ወቅት በርዕስ ወይም ዘዉግ ላይ ተመስርቶ የክፍል የግጥም አፈ ታሪክ እና የግለሰብ አፈታሪክ ሲጽፉ በዊልያም እና በሜሪ ዩኒት (William and Mary unit) ውስጥ ያለው ግጥም እና ተጨማሪ ስብስቦች ለመተንተን እንደ አማካሪ/ረጂ ጽሑፍ ሆነው ያገለግላሉ። በታተሙ የደራሲያን ልዩ የእጅ ሙያ እንቅስቃሴዎች ላይ የትምህርት ማዕከሎች እና በርካታ የግጥም ዓይነቶች በሚጽፉበት ጊዜ የማያቋርጥ ክለሳ ይደረጋል።<br><br>ተማሪዎች ለአሳማኝ ጽሑፍ የዊልያም እና ሜሪ ሃምበርገር ሞዴልን በመጠቀም በመረጡት ርዕስ ላይ መጣጥፎች ለማዘጋጀት ስለ አሳማኝ አጻጻፍ የተማሩትን ሁሉ ይጠቀማሉ።<br><br>ተማሪዎች ከማህበራዊ ጥናቶች ትምህርት ሪሶርሶችን፣ ቪዲዮዎችን፣ ዋናዎቹን ምንጮች፣ እንዲሁም የህትመት እና ዲጂታል ጽሑፎች የሚጠቀሙበትን፣ በዌስትዋርድ መስፋፋት ርዕስ ላይ የራሳቸዉን የታሪክ መነጽር/The Lens of History፦ የስነ-ታሪክ ምርምር ዘገባዎች አፃፃፍ ዩኒት ይጀምራሉ። ተማሪዎች በዩኒት 2 ውስጥ በተማሩት በፍጥነት፣ የትኩረት ምርምር እና በማስታወሻ-መውሰድ ለመሳተፍ በምርምር ቡድኖች ውስጥ ይሰራሉ። ከዌስትዋርድ መስፋፋት ዉስጥ በተወሰነ ንዑስርዕስ በፍላጎት የሚቀርብ ዘገባ የመጨረሻው ዉጤት ነው። | ተማሪዎች የዊሊያም እና ሜሪ የለውጥ ስርዓት/ቅጥ/ፓተርን ዩኒትሲያጠናቅቁ እንዲሁም የዊልያም እና የሜሪ የምርምር ሞዴልን በመጠቀም በምርጫ ርዕስ ላይ በተመረኮዘ የምርምር ፕሮጀክት ላይ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች በቃል የሚያቀርቡት፣ሪፖርታቸውን በሚጽፉበት ጊዜ ሁሉ በሪፖርታቸው ላይ ምርምር ሲያካሂዱ ንባቡ እና ጽሑፉ በጥብቅ የተገናኙ ናቸው። ተማሪዎች እድገቱን ከመጀመሪያ ግምገማ ጋር ለማነፃፀር የድህረ ምዘና ግምገማ በመውሰድ የዊልያም እና የሜሪ ዩኒትን (William and Mary unit) አጠናቅቀዋል።<br><br>በጽሑፍ ውስጥ አንዱ የመጨረሻዉ የሉሲ ካልኪንስ የጥናት ዩኒት/ክፍል፣ጽሑፍን ቅርጽ ማስያዝ፦ ከመጣጥፍ እና ከትረካ ወደ ግለታሪክ፣ በዩኒቱ እና በዓመቱ የመጨረሻ ሳምንታት ወቅት ትምህርት ይሰጣል። ተማሪዎች ወደ መካከለኛ ት/ቤት ሽግግር ሲጀምሩ መምህራን ይህንን ግለታሪክ በ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ተሞክሮ ላይ ለማተኮር ሊመርጡ ይችላሉ። |

© 2019 ፈጣንና የዳበረ ትምህርት